Finote Ethio-Canadian Information Centre In Toronto
ፍኖተ ኢትዮ-ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከል በቶሮንቶ
E-mail: torontofinote@gmail.com

# አፈ ቅቤ ልቡ ጩቤ የኢህአዴግ ጠ/ሚ ኮሎኔል አቢይ አህመድ እውነተኛ ማንነት

## ኢትዮጵያን አልላቀቅ ያላት የጸረ ኢ/ያ የጥፋት ዓላማና ትብብር

የኢትዮጵያ የውስጥ ጠላት ሆነው ያቺን ቅድስት፣ ጥንታዊና ታሪካዊ አገር በውጭ ጠላቶቻችን ሴራና ድጋፍ አማካኝነት ሊያጠፉዋት የተነሱት ሻዕቢያ፣ ወያኔና ኦነግ በስልታዊ ቡርቦራና ግልጽ ጦርነት፣ በግልና በጋራ ወስጥ ውስጡን ሲያደሟትና ሲገዘግዟት ለብዙ ዓመታት ቆይተዋል፡፡ ዓላማቸው ግልጽ ነበር፤ ኢትዮጵያን መበታተን እና ብዙ አናሳ አገሮችን መፍጠር ነው፡፡ ይህንን ዓላማቸውን ደብቀው በነጻ አውጭ ስም ወገንን ከወገን ሲያጨራረሱ፣ የሩቅና የጎረቤት ጠላቶች በሚያደርጉላቸው ድጋፍና መጠለያ ሲያመቻቸው የገጠር ከተማ ሲቆጣጠሩ፣ በኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል ሲጠቁ ደግሞ ወደ ጎረቤት አገር በመሸሽ ድካማቸውን ሲወጡና ሲጠናከሩ ቆይተው እየተመለሱ አገራቸውን ሲያደሙ ኖረዋል፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ መከላከያና ሕዝብ ብዙ መስዋዕትነትን ከፍለዋል፡፡ የንጉሱንና የደርግን ስርዓት ለመታገል የተሰለፉ ወጣቶችና ተማሪዎች ባለማወቅ የነርሱ ፕሮፓጋንዳ አራማጅና መጠቀሚያም የሆኑበት ወቅትም ነበር፡፡

ከነዚህ ጠላቶቻችን አንዱ የሆነው ከጥንስሱም፣ ከእድገቱና በሂደቱም ጸረ ኢትዮጵያ የሆነው ኅወሓት/ወያኔ  በለስ ቀንቶት በአሜሪካ ቡራኬነት ጀሌዎቹን ሰብስቦ አዲስ አበባ ከገባበት ግንቦት 1983 ዓ/ም  አንስቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልደረሰበት ፈተና፣ ስቃይ፣ ጥፋት፣ እልቂትና ፈተና የለም፡፡ በሕዝቡ ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ፣ የዘር ማጽዳት ወንጀል በተለይ በአማራው ላይ የተካሄደበት፣ ህዝብ መጤ እየተባለ የተፈናቀለበት፣ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በጥቂት ቀኖች ጦርነት ከ 100 ሺህ በላይ ህዝብ የተማገደበት፣ ወጣትና ምሁሩ የተሰደደበት፣ አብሮ የኖረና የተዋለደን ሕዝብ በቋንቋና ጎሳ ተከልሎ የተለያየበት፣ ታሪክ ተደልዞ የሀሰት ታሪክ የተጻፈበት፣ ሰርዓተ ትምህርቱ ወድቆ ትውልድ ለድንቁርና የተዳረገበት፣ አኩሪው ባሕል የጠፋበት፣ ትውልድ በሱስና በጎጂ ልማዶች የተዘፈቀበት የወደፊት አገር ተረካቢው አገር አልባ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ይህም የሕይወት ጥፋት፣ የታሪክ፣ የትውልድ፣ የስነልቦና፣ የባሕል፣ የማህበራዊ ኑሮ፣ የመሬትና የአየር ብክለት ወዘተ ... እያለ በሁሉም መስክ ጥፋት ሲካሄድና የውድቀት ሩጫ ሲያሳይ፤ ባለጊዜዎቹ ወያኔዎች ደግሞ ሲገቡ ቡቱቷቸውን አጥበው ተባዩን ለማራገፍ  ቤተመንግሥት አጥር ላይ ለጸሐይ እንዳላሰጡ ሁሉ፤ በአንድ ጀምበር አዳር የህንጻ ባለቤትና ባለ ቱጃር የሆኑበት፣ የሀገሪቱን ሀብት አግበስበሰው የዘረፉበትና ካገር ያሸሹበት፣ ለውጭ ከበርቴዎች መሬት በሊዝ (በነጻ ማለት ይቻላል) ተሰጥጧቸው የዘረፉበትና የከበሩበት፣ በልማት ስም ምድሩ፣ አየሩ፣ ውሃው ለብክለትና ለአደጋ የተጋለጠበት፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ወደፊት ብዙ አደጋዎችን ሊያስከትሉ የሚችሉ ፋብሪካዎችና የይድረስ ይድረስ ሰራዎች የተካሄዱበት አገር ስትሆን፤  ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተረፈው ነገር ቢኖር፤ በበጀት ድጎማ ኢኮኖሚ የተመራበት፣ የብድር እዳና ተመጽዋቾችነት ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ ብዙ ፈተናዎችን ያሳለፈ ታላቅ ሕዝብ ስለሆነ ሁሉንም መከራ ችሎ፤ እየታገለ ያለው ታግሎ፣ የተሰዋው ተሰውቶ፣ ሌላው የቁም ስቃይ ተሰቃይቶ፣ ከፊሉ ተሰዶ 27 የግፍና የመከራ አመታትን አሳልፎ በሕዝብ ተቃውሞና ትግል የወያኔ ሥርዓት ሊገረሰስ አፋፉ ላይ ሲደርስ ደግሞ ፤ የኢትዮጵያ ጠላቶች መክረውና ዘክረው ተጋጀተውበት አገሪቱ ከቁጥጥራቸው እንዳትወጣ ሰዎችን በመለወጥ ሰርአቱን ለማስቀጠል ያዘጋጁትን ሰው የለውጥ አርበኛ አድርገው አመጡልን፡፡ ኮሎኔል አብይ አህመድን! ዛሬም እንደትላንቱ የኢትዮጵያ ጠላቶች  ሻዕቢያ፣

አነግና ወያኔ/ህወሃት አንዱ ከሌላው እየተባበሩ ከሌሎች ጀሌዎቻቸው ጋር እያሴሩብን፣ እያጠፉን ናቸው፡፡ ልብ አድርጉ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ሳይሆን ድርጅቶቹ ሕዝብን እያወናበዱ መጠቀሚያ እያደረጉ መሆኑን መጤን አለበት፡፡

### ለውጥ መጣ ተበሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳግም የተታለለበት የአብይ አህመድ አገዛዝ

ከኢሕአዴግ ወስጥ ባለ ተረኛ አድርገው የኦህዴድን/ ኦዴፓ የተባለውን ቡድን በጎወሓት ተክተው 'የለውጥ ነጋሪት' አስመትተው የተዋጣለት ድራማ ተጫዋቹን ኮሎኔል አቢይ አህመድን ካስቀመጡት ሁለት አመት ሆነው፡፡ ያዘጋጁት ሰው መሆኑን ለማስታወስ የአሜሪካው የወጭ ጉዳይ ኃላፊ አዲስ አበባ  በማርች 2018 ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደረስ ለኢህአዴግ ተሰብሳቢዎች አቢይ አህመድን ለጠቅላይ ሚኒስትርነት እንዲመርጡ መናገሩን አይዘነጋም፡፡ አዎን 180 የኢሕአዴግ አባላት ተሰበሰበው ጠቅላይ ሚኒስትራቸውን መረጡ! ልብ በሉ የወያኔው ሰርዓት ቁንጮው ነው ጠቅላይ ሚኒስትራቸውን የመረጡት እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም! መለስ ሲሞት በኃይለማርያም፣ እርሱ ወረድኩ ሲል ድግሞ ወያኔውን አቢይ አህመድን፡፡ ሌላ ታሪክ የለውም፡፡ አቢይ አህመድን ከዚያ በፊት በወታደርነቱም ሆነ በሰለላ ተቋም ሲሰራ በሚዲያ ድምጹ  ተሰምቶ ሰሙ ተነስቶ የማይታወቅ ሰው ስለነበር ለድራማው የተስተካከለ ጥሩ ተዋናይ ሆነላቸው፡፡

አብይ አህመድ በ15 አመቱ የኦነግ ጀሌ ሆኖ ለ3 አመት የጥፋት ተልኮ ሲያካሂድ የነበረ ነው፡፡ አቢይ በአፋኙ፣ ገዳዩ፣ አስቃዩ፣ አሳዳጁ ደህንነት ወስጥ ሲሰራ የነበረ ወታደር መሆኑን መዘንጋት የለበትም፡፡  ከ 15ቱ  ዓመቱ እስከ 42 ዓመቱ ድረስ ለ 27 ዐመት በጥፋት ጎዳና የነበረን ሰው በአንድ ወር የቴሌቭዥን ፕሮፓጋንዳና በ27 ደቂቃ የፓርላማ ንግግሩ 'የለውጥ መሪ  አርበኛ' ወይም 'የቲም ለማ ቡድን' ተበሎ ልብሱን አስማምሮ ብቅ ሲል 'ከላይ የተላከ መሪ' አድርገን አጨበጨብን፡፡ በስህተት ተታለልን፡፡ ለዚያም ስህተታችን አሁን ዋጋ እየከፈልን እንገኛለን፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም መሪ ቸግሮት በመለስ ዜናዊ ጸረ ኢትዮጵያ ስድና ብልግና አነጋገር፣ አፋኝ ና አምባገነን አገዛዝ ሲመረር ቆይቷል፡፡ ባለው ከፋፋይ ሕገ መንግሥት፣ በቋንቋና ጎሳ በተካለለ ፌዴሬሽን፣ በአፋኝ ሰራት፣ ፍትሕ በለሌበት፣ የሕግ የበላይነት ባልሰፈነበት አገር ወስጥ ወያኔው አብይ አህመድ 'ኢትዮጵያ' 'ኢትዮጵያ' ሰላለ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ተገርሞና ተደንቆ እውነተኛ መሪ አገኘን ብሎ ተታለለ፡፡ የውስጥና መሰረታዊ የሰርዓት ለውጥ ሳይሆን ሕዝብ ማየትና መስማት የጠላቸውን ሰዎች ከቤተመንግስት ገለል በማድረግ፣ የተወሰኑ እስረኞችን በመፍታት፣ ሚዲያውን ለቀቅ በማድረግ ስራቸውን ሳይሆን ፊታቸውን ቀይረው  አነጋገራቸውን አሳምረው ስለመጡ ለውጥ የመጣ መሰለን፡፡ የቸገረን እኮ ሰው ሳይሆን የሰርዓት ለውጥ መሆኑ ጭራሽ ተዘነጋን፡፡ጉድ በል አለ ጎንደር!

ታዲያ እጅግ ብዙ አዋቂ ምሁራን፣ ታላላቅ ሰዎች፣ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች፣ የሃይማኖት አባቶች እውቅ ኢትዮጵያውያን እንዴት ተታለሉ? እንደምንስ ይህን አይነት ሰህተት ሊሰሩ ቻሉ? ቢባል መልሱ ቀላል ነው፡፡ የቸገረው እርጉዝ ያገባል ተረት አይነት ሆኖባቸው፤ ፊት ለፊት የሚታዩትን ሕዝብ የጠላቸውን ወያኔ ባለስልጣናትን አስወግዶ 'ኢትዮጵያ' ብሎ የሚጠራ ሰው ሰለሰሙና በንግግሩ ሰለተመሰጡ፣  'ኑ አብረን እንስራ እንደመር'፣ 'ሰንኖረ ኢትዮጵያዊ ሰንሞት ኢትዮጵያ' የሚለውን አባባል ሰለተናገረ እውነት መስሏቸው አምነውት እንጂ አብይ ምን አይነት ሰው ነበር? ለ 27 ዓመት ምን ሲሰራስ ነበር? የሚለውን ከማጣራት ለካስ ከመካከላቸው ለውጥ ፈላጊም አለ በሚለው  ሊሆን ይችላል፡፡ በተለይ በውጭ ለብዙ ዓመታት የኖሩ ትወልደ ኢትዮጵያዊያን ለሀገራቸው ባላቸው ፍቅርና ለሕዝባቸው ሰላምና እድገት ጽኑ ፈላጎት ነው፡፡ የወስጥ አርበኞችና በግርግሩም ስልጣንና ልዩ ጥቅም የፈለጉም ሰለነበሩ ለውጥ መጣ መባሉን ጥሩ አጋጣሚ ተገኘ በለው ያልተቆጠበ ጭፍን ድጋፋቸውን ሰጡ፡፡ ከዚያ በሁዋላ የማህበራዊ ሚዲያው መጦዝ እና የሁሉንም አእምሮ በረዘው፣ የመጠራጠር አቅማቸውን ሰለበው፡፡ እንደተለመደው 'አብይ' 'አብይ' የሚል በዛና አጋፋሪ ለመሆን እርብርቡና ጥድፊያው ሽኩቻው ተጧጧፈ፤ ጮሌው አበይም ሁሉም እንደልቡ እንዲናገር ለቀቅ አደረገው፡፡ እውነት ነው ብሎ ተቃዋሚ የተባለው ሁሉ  ከአንድ ወይ ሁለት ድርጅት በቀር ሌላው የአወሮፕላን ተከፍሎለት የሆቴል ወጪው ተችሎት አገር ቤት ገባ፣ ጉድ ተባለ፤ ፖለቲካ አዋቂ ነኝ ያለ ሁሉ በአንድ ሆቴል ውስጥ

ተቀምጦ የአብይ የስለላ መረብ ቋት ወስጥ ገባ፣ ስልኩ ስበሰባው አጀቡ ሁሉ ባይን ቁጥጥር ስር ሆነ! አቢቹ ሰራውን ስራ! ምን ችግር አለው? ለብዙ አመታት ተቃውሞ ሲያሰማ የነበረ የውጭው ሲኖዶስ የሃይማኖት አባቶች ዋሽንገተን ዲሲ ለሰበሰባ በሄዱበት ልብስና ሻንጣ 'ኑ ከእኔ ጋር ካልሄዳችሁ' ብሎ በአንድ አወሮፕላን በመንግሥት ወጪ ይዟቸው ነጎደ! አወሮፕላን ወስጥ እየተዘዋወረ ፎቶ ተነሳ!  አገር ጉድ አለ! አብይ የተከፋፈሉትን ኦርቶዶክሱን አስታረቀ እና ሙሰሊሙን ችግራቸውን ፈታ ተባለለት፡፡ አጅሬ ተቃዋሚወን ሁሉ ሰብስቦ ማኖ ካስነካ በኋላ የራሱን ሰራ መስራት ጀመረ፡፡

አሥመራ ሄዶ ጸረ ኢትዮጵያዊውን ኦነግ ን በወስጥ ድርድር ወደ ኢትዮጵያ አስገባ፡፡ ኦነግ ቁርስና ምሳውን ወያኔ መቀሌ አብልቶ ሴራ ጎንጉኖ አስታጥቆ አስገባው፡፡ ተቃዋሚ ከነመሳሪያው አገር ቤት ድንበር አቋርጦ የገባባት አገር ኢትዮጵያ ብቻ ነች፡፡ ተዳክሞ ስሙ ብቻ ቀርቶ የነበረውን ኦነግ  ዳውድና ከማል ገልቹ አሳሪና ታሳሪ ሆነው አስመራ እንዳልከረሙ ሁሉ አሁን እስካፍናጫቸው ታጥቀው፣ በጠባቂ ታጅበው፣ ተጠናከረው ጃዋርን የመሰለ አሽባሪ እንደልቡ እየፈነጨ አገሪቱዋን የጥፋት፣ የሽብርና የዝርፊያና የስጋት አወድማ አደርጉዋት፡፡

## አብይ አህመድ የአማራና የኢትዮጵያ ጠላት ነው

ለጥፋት ኢላማ የሆነው አማራ እና የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ግን ፈተናና መከራቸው እያደረ በረታ አደጋ ላይ ወደቀ እንጂ ምንም የወረደ ነገር የለም፡፡ ከ6 ወር በፊት እነ ጄኔራል አሳምነው ጽጌን፣ ዶ/ር አምባቸውን እና ሌሉቹን አመራሮች ሲያስገድል አብይ የመራው፣ ያቀነባበረው የብዙ ጠላቶችን አላማ ያሳካበት እርምጃ ነበር፡፡  ረጋ ብላችሁ አስቡ ቤተክርስቶያኖች ሲቃጠሉ፣ ኢትዮጵያዎን በየቦታው ሲታረዱ፣ አማራው መጤ እየተባለ በኦሮሚያ፣ ቤንሻጉል እና ሶማሌ ክልል ሲገደል ባንጻሩ 18 ባንኮች ሴዘረፉ በሚሊዮን ሰዎች ተፈናቅለው ሲሰቃዩ አብይ አህመድ ያደረገው የተናገረው ነገር ነበርን? በቅርቡስ ጃዋር ባነሳሳው ሽብር 86 ንጹሃን ሲገደሉ ሲታረዱ ሲቃጠሉ አብይ በቴሊቢዥን መስኮት መጥቶ 40 ኦሮሞ ይህን ያህል እስላም ይህን ያህል አማራ ደቡብ ተገደሉ በሎ ጎሳቸውን ሲጠቅስ ምን ማለቱ ነበር? የማንን ወንጀል ለመደበቅ ነበር እንደዚያ ያለው? 17 የዩነቨርስቲ ተማሪዎች ታግተው ሁለት ወር ደብዛቸው ሲጣፋ ካፉ ቃል አውጥቷል? እኔ የሚያስፍራኝ የአማራ ብሄረተኝነት ነው ማለቱስ ለምን ይሆን? |መከላከያው፣ ልዩ ኃይሉ፣ ደህነንቱ ሁሉ በአንድ ቡድን ወስጥ ሲሆን ምንን ኢያሳየ ነው? ኦንጎች ምናልባት ቶሎ ኢትዮጵያን አጠፍተን ኦሮሚያን እንመስረትና እንኑር በሚለው አከራሪና የለም ቀስ በቅስ እየገዘገዝን ብሚለው ከፍል ሽኩቻ በመሃላቸው ሊኖር ይችል ይሆናል እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብና አገር ግን በጠላትነት ሁሉም አንድ ላይ አድሞ ተነስቷል፡፡

## የሕዝብና የጠላት ጎራ ለይቷል ትግሉ ተፋፍሟል

አሁን ያስቸገረን የራሳችን ጠማማ ነው ብለዋል ዛፎች፡፡ አሁን ያስቸገረን 'ለጠቅላይ ሚኒስትር አብይ እድል እንስጥ'፣ 'ሌሎቹ አላሰራ ብለውት ነው'፣ 'ተስፋ አንቆርጥም'፣ 'ይህን ያርግ' እየተባለ በሌላው ኢትዮጵያዊ የሚደረግለት የአድር ባይነት ድጋፍና ማዘናጋት እንዲቆም ነው፡፡ የኢትዮጵያን ጠላት የደገፈ የኢትዮጵያ ጠላት ነው፡፡ ዶክተር እከሌ ፕሮፌሰር እከሌ፣ አርቲስት እከሌ፣ ባለሃብት እከሌ፣ ዲያቆን እከሌ እየተባሉ ህዝብን የሚያዘናጉ አድርባዮችና ፈሪዎች ወይም ጥቅመኞች አቋማቸውን ያስተካክሉ፡፡ ቤተመንግስት እራት መብላት እንደ ሕዝብ ነጻነት የሚቆጥሩ ሆዳሞች፣ አብይ ጋር ፎቶ መነሳት ባለስልጣን ያደረጋቸው የሚመስላቸው መስመራቸውን ያስተካክሉ፡፡

አብይ ጸረ ኢትዮጵያ፣ የወያኔ ሰርዓት አስቀጣይና የውጭ ጠላቶች መሳሪያ ሰለሆነ፤ ሕዝብ መስመሩን ለይቶ ይታገላል፡ የአብይ ሎሌ ሆነው አማራውን የሚያስጠቁ የአዴፓ መሪዎችና አባላት ከእርሱ ተለይተው አይታዩም፡፡ ተቃዋሚ ነን ብለው የአብይን ሰልጣን የሚያራዝሙና ፈርፋሪ ለቃሚዎች አብረው በአንድ ሙቀጫ መግባታቸውን ይወቁት፡፡

ኢትዮጵያን ለማዳን ኢትዮጵያዊው ሁሉ በአንድ ጎራ፣ ጠላት በሌላው ጎራ ሆኖ ፍልሚያው ይቀጥላል፡፡ ጠላትና ወዳጅ ተለይቱዋል፡፡ የሻዕቢያ፣ የወያኔና ኦነግ ሴራና አገር ማጥፋት በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ይከሽፋል! ይደመሰሳልም፡፡ ለሆድህ፣ ለስልጣን ፍርፋሪ የቆመጥክ ሁሉ አገር ከሌለህ የት ሆነህ ልትበላ? ልትጠቀም? መስመርህን ለይ!

**ማጠቃለያ**

አብይ ማን እንደሆነ፣ ምን እንደሚሰራ ካወቅን መቃወሙ ብቻ ዋጋ የለውም፡፡ መፍትሔው ኢትዮጵያዊው ሁሉ በአንድ ዓላማ ማለትም ኢትዮጵያን ለማዳን ቆርጦ መነሳት፤ የሰረዓት ለውጥ እንዲመጣ መታገል፤ በዘርና በሃይማኖት መከፋፈልና መቧደንን ትቶ በኢትዮጵያዊነት መንፍስ መሰባሰብ፣ በዚያም አቅጣጫ መጓዝ፤ ኢትዮጵያን ሊታደግ የሚችል ሕዝባዊ ሰርዓት ሊዘረጋና ሰላምና ዲሞክራሲን ሊያሰፍን የሚችል ከሁሉም የሕብረተሰቡ አካል የተውጣጣ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት መመስረት ብቻ ነው፡፡ መፍትሄው በአሜሪካ፣ አውሮፓና አረቦች እጅ ሳይሆን በእኛው በኢትዮጵያውያኖች እጅ ነው፡፡ ይህንንም ለማድረግ የምንችለው ስንደራጅ ነው፡፡ አዎ ያለተደራጀን መቶ ሚሊዮን ሕዝብ የተደራጀ ጥቂት ሺዎች ሲጫውቱበት ማየት በቃ ማለት አለብን! ግልጽ ዓላማና ግብ ይዘን እንሰባሰብ እንደራጅ! ተደራጅተንም እንታገል፣ ታግለንም እናቸንፋለን፡፡

ኢትዮጵያ በጀግችና ቆራጥ ልጆቿ ትግል ተከብራ ትኖራለች!
ሞት ለሻዕቢያ ወያኔና ኦነግ!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!